# ስፖርት

## ባህልን በገና ጨዋታ

ብርሃን ፈይሳ

በበርካታ ባህል የበለጸገችው ኢትዮጵያ ከእሴቶቿ መካከል ባህላዊ የስፖርት ጨዋታዎችና ፉከክሮች ይጠቀሳሉ። በተለይ በዓላትን ተገን አድርገው፤ መንደር ከመንደር፣ ደብር ከደብር፣ ላይ አምባ ከታች አምባ፣... ከሚፎካከሩባቸው ውድድሮች መካከል የገና ጨዋታ አንዱ ነው። ይህንን ጨዋታ ወጣቶች ተሰባስበው መኸር በተሰበሰበበት ለጥ ያለ ሜዳ ከታህሳስ ወር ጀምሮ በጥር፣ በሚያዚያ እስከ ክረምቱ መግቢያ ድረስ የሚጫወቱት መሆኑንም በኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን የተዘጋጀ ሰነድ ይጠቁማል።

ዛሬ የሚከበረውን የገና በዓል ምክንያት አድርገውም የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ከመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ጋር  የቡድን አባቶቻቸውን ይዘው በመቅረብ እንደ ወጉ ‹‹ነብሮ›› እና ‹‹አምበስ›› በሚል ተሰይመው በጃንሜዳ ውድድራቸውን አድርገዋል። በባህል ልብሶች አሸብርቀው ከጫፉ ቀለስ ባለው የገና ዱላ ሩሯን(ጥንግ) እየለጉ ቢፎካከሩም መሸናነፍ ባለመቻላቸው በመለያ ምት የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ረተው የበግ ተሸላሚ ሆነዋል። በመጨረሻም ሁለቱም ቡድኖች ‹‹አሲና በል አሲና ገናዬ›› እያሉ በመዝፈን ተለያይተዋል።

የኪነጥበብ ባለሙያዎችን ወክለው በጨዋታው ከተሳተፉት መካከል አንዱ አንጋፋው አርቲስት ፋንቱ ማንደዬ ናቸው። ገናን እየተጫወቱ ያደጉ ሲሆን፤ ጨዋታው የባህል መገለጫ እንደመሆኑ ሊጠናከር እንደሚገባው ያሳስባሉ። ሽልማት ያላቸው ውድድሮችን በየአካባቢው በማዘጋጀት ማስፋፋት እንደሚቻልም ይጠቁማሉ። ሌላኛው አንጋፋ አርቲስት ችሮታው ከልካይ በበኩላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን የውጭ አገራት ነዋሪዎች (ዲያስፖራዎች) በተጠሩበት በዚህ ወቅት ባህልን



**የኪነጥበብ ባለሙያዎች ከመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ጋር ያደረጉት ጨዋታ፤**

እንዲሁም አገሪቷ ያለችበትን ሁኔታ ማሳየት መልካም እድል እንደሆነ ይገልጻሉ።

‹‹በዚህ ውድድር ላይ መሳተፍ ለሌላው አርዓያ ከመሆን ባለፈ ለዲያስፖራው ማህበረሰብ ኢትዮጵያ ከእነ እሴቶቿ  እንዳለች ለማሳየት፣ የውሸት ፕሮፓጋንዳውም ተጨባጭ ያልሆነ መሆኑን እንዲረዱ የሚያግዝ ነው። ስለ አዲስ አበባ ከተማ አሉታዊ መረጃ ሲያስተላልፉ ለቆዩትም ጥሩ ማሳያ ይሆናል። በቀጣይም መሰል ውድድሮችን በወጣቶችም ሆነ በባህልና ቱሪዝም ቢሮ በማዘጋጀት ስፖርቱን ማሳደግ አስፈላጊ ነው›› ሲሉም አሳስበዋል።

የጋዜጠኞች ቡድንን በአምበልነት የመራው ጋዜጠኛ ነዋይ ይመር፤ የገና ጨዋታ አስደናቂ ህግ ያለውና አስደሳች የሆነ ጨዋታ መሆኑን ይጠቁማል። ገናን ጨምሮ የባህል ስፖርቶች በሚፈለገው ልክ እንዲያድጉ የሁሉም ኃላፊነት ሲሆን፤ የመገናኛ ብዙሃን ግን ከሙያቸው አንጻር ከፍተኛ ስራ መስራት አለባቸው። ስፖርቱን የሚመሩት አካላትም ህብረተሰቡ ጋር ተደራሽ የሚሆንበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባቸዋል። ‹‹በርካታ ስፖርቶችን ከውጭ እንደመዋሳችን እኛም ለውጪዎች ልንሰጣቸው የምንችላቸው ስፖርቶች አሉ። በመሆኑም ስፖርቱን በማበልጸግ ወደ ተሻለ ደረጃ ማሸጋገር አስፈላጊ ነው›› ብሏል።

ሌላኛው ጋዜጠኛ አንተነህ ሲሳይ በበኩሉ፤ በልጅነት የሚያውቀውን የገና ጨዋታን ለረጅም ጊዜ ሳይጫወት መቆየቱን ያስታውሳል። ህግ ተዘጋጅቶለት በዚህ መልክ መካሄዱም እጅግ ደስ የሚል ነው። በርካታ ባህላዊ ስፖርቶች በኢትዮጵያ ቢኖሩም ውድድር ለማካሄድ ገናን መጠበቅ የለበትም። ከገና ጋር ተመሳሳይ የሆነው የፈረንጆቹ ‹‹ሆኪ›› ህግና ደንብ ተዘጋጅቶለት በመካሄዱ ታዋቂ ስፖርት ሆኗል።

ራሳቸውን ከማስተዋወቅ ባለፈም በገቢ ተጠቃሚ ሆነውበታል። በመሆኑም እንደ ገና ያሉ የባህል ስፖርቶችን በማሳደግና በማስተዋወቅ ከፍተኛ ስራ መስራት የግድ ነው፤ ለሌሎች ስፖርቶች የሚሰጠውን ያህል ትኩረት መስጠትም ያሻል። የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች፣ አንጋፋ ሰዎች እንዲሁም ባለሃብቶችም ስፖርቱን ማስተዋወቅ እና ማገዝ ይገባቸዋል ሲልም መልዕክቱን አስተላልፏል።

ማስተር ሄኖክ መገርሳ ለሁለት አስርት ዓመታት አሜሪካን ጨምሮ በተለያዩ አገራት የኖሩ ዲያስፖራ ናቸው። ገናን ልጅ ሆነው መጫወታቸውን አስታውሰው ይህንን መሰል ውድድር ማካሄድም ዘርፈ ብዙ ፋይዳ እንዳለው ይጠቁማሉ። ይህ ጨዋታ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተወራረሰ መቀጠሉን በመመልከታቸው መደሰታቸውን ጠቅሰው፤ ዓለም አቀፍ ፌስቲቫል እንዲሆን መሰራት ይገባዋል። ዲያስፖራው ማህበረሰብም ባህሉን እንዲያውቅ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎችን ማከናወን እንደሚያስፈልግም አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ብርሃኑ አድማሱ፤ ትውልዱ ባህሉን እንዲያውቅ ትምህርት ቤቶች ላይ መሰረት በመጣል በፕሮጀክቶች ታቅፎ ታዳጊዎች እንዲሳተፉበት እየተሰራ መሆኑን ይገልጻሉ። በከተማዋ 11ዱም ክፍለ ከተሞች ፕሮጀክቶች የተመሰረቱ ሲሆን፤ የአገሪቷን እሴት የማስተዋወቅ ስራ እንደመሆኑ ትምህርት ቢሮ እንዲሁም የባህልና ቱሪዝም ቢሮ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ትኩረትና እገዛ ሊያደርግ ይገባዋል። ስፖርት ቢሮውም የተለያዩ መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት እንደሚገባውም ጠቁመዋል።

ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# እንኳን ለብርሃነ ልደቱ በሰላም አደረሳችሁ!

የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለእየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ በማለት በዓሉ የሰላምና የደስታ እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቱን ይገልጻል። ድርጅታችን አለም አቀፍ የጥራት ሥራ አመራር ስርዓትን በመተግበር በአገር አቀፍ ደረጃ የትራንስፖርት ዘርፎች ብቸኛው ISO-9001-2015 ሰርተፍኬት ማግኘት በመቻሉ ከቡራን ደንበኞቻችን ጥራት ያለው አገልግሎት ማግኘት መቻላቸው መሆኑን እናበስራለን። እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን ደስ ያለን!!

ድርጅቱ በአዲስ አበባ ከተማ  በፌዴራልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለሚሰሩ ሠራተኞች በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች አገልግሎት ይሰጣል። እንዲሁም ከሥራ መግቢያና መውጪያ ሰዓቶች በውጪ በበዓላትና በእረፍት ቀናት ለሌላው የኀብረተሰብ ክፍል የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በተመጣጣኝ ታሪፍ በመስጠት ወጪውን በመቀነስና ገቢውን በማሳደግ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው አገልግሎቶች በመስጠት ላይ ነው።

በተጨማሪም በቅርቡ የማንኛውም ዓይነት የተሽከርካሪ ሰሌዳ የማተምና የማሰራጨትን ኃላፊነትን ከፌዴራል ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር በውክልና ተረክቦ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆን፤ ስራውን የተቀላጠፈና ከብልሹ አሰራር የፀዳ ለማድረግ ሲባል የጠፋ የተበላሸና ምትክ ሰሌዳ የሚፈልጉ ደንበኞች ሰሌዳውን ባወጡበት የትራንስፖርት ቢሮ በኩል መስተናገድ እንዲችሉ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። በመሆኑም አገልግሎቱን የምትፈልጉ ደንበኞች ሰሌዳውን



ባወጣችሁበት ቢሮ በሕጉ መሠረት አስፈላጊውን መረጃ ይዛችሁ በመቅረብ አገልግሎቱን ማግኘት ትችላላችሁ።

ድርጅቱ ተቋቁሞ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን የተጓዘበትን የዕድገት ደረጃ ስንመለከት በርካታ ስኬቶች እያስመዘገበ በስኬት ላይ ስኬትን እየደረበ በመሄድ ላይ ያለ ድርጅት ነው። ባሳያቸው



ECAE CD
CERTIFICATE
ES ISO 9001:201
The ECAE CD of the
Ethiopian Conformity Assessment Enterprise
hereby certifies that

Public Service Employees
Transport Service Enterprise
Address of Company
ead office: City/Town: Addis Ababa, Sub-City: Lideta, Wereda: 10,
Phone No: +25115155159, Email:psetse2@gmail.com
ranch location: East(Ayat side),West(Jemo site),North(Winget side) and
South (kality site)branches in Addis Ababa,Ethiopia.

has established and applied a quality system for

Transport Service for Employees of Federal and Addis Ababa City dministration, Render a public transport Services for the Society living in Addis baba City Administration, Contract Transport Services, Vehicle Maintenance nd Inspection."

which conforms to the requirements of the
International Management Systems Standards, ISO 9001:2015

04 Jan. 2022
Certification Date

03 Jan. 2025
This certificate is valid until

Certificate Registration number: QS/0094
Issue No. 01, Issue Date: 04 Jan. 2022

Amsalu Enyew
Certification Director
Director, Certification

CMS Certification Body CMS0001
Page 1 of 1

Addis Ababa, Ethiopia
+251 11 646 0548/37
Fax: +251 11 646 0880/81

ከፍተኛ መሻሻሎች  በአገር አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ጥራት ሽልማት ድርጅት ባካሄደው ውድድር ሦስተኛ ደረጃ የዋንጫ ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል።